ቀን፡ 29/03/2015

**በስመ አብ፤ ወወልድ፤ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሃዱ አምላክ አሜን!!**

**ባህረ ሐሰቱን የምንሻገርበትን የእውነት መርከብ ማን ይሰጠናል? ወዳጄ ሆይ፡- አትፍራ! እውነት አባትህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐ. 14÷6)፡፡ እርሱ « *መንገድም ፣ እውነትም ፣ ሕይወትም* » ነው፡፡ መንገድ ነው፡- ትሰማራበታለህ፣ እውነት ነው ፡-ትይዘዋለህ፣ ሕይወት ነው፡- ትኖረዋለህ !!!**

የርዕሰ አድናራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ ሁኔታ።

በእንግሊዝ ሃገር የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ስደተኛ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ገንዘብና ጉልበቱን አስተባብሮ በእግዚአብሔር ተራዳዒነት የገዛውን ህንፃ ቤተ ክርስቲያን ለወያኔ ሹማምንት አሳልፈው በመስጠት ሥልጣንና ንዋይን የሚያጋብሱ የመሰላቸው የለንደኑ ዳያብሎስ አባ ግርማ ከበደና ተከታዮቻቸው፤ የቤተ ክርስቲያኑን አባላት መብት የሚነፍግ ተግባር ፈጽመው አባላቱ በቤተ ክርስቲያኗ ንብረት እኩል የመገልገል መብታቸው እንዲከበርላቸው ጉዳያቸውን ወደ ፍርድ ቤት ወስደው በ13/02/2013 በዋለው የእንግሊዝ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ችሎት ተፈረደላቸው።

ይህንን አስመልክቶ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያስተላለፈውን ውሳኔና ያወጣውን ትዕዛዝ (interim relief order ) አባ ግርማና ተከታዮቻቸው ተግባራዊ አናደርግም በማለታቸው የፍርድ ቤትን ትዕዛዝ ባለማክበረ (በContempt of Court) ተከሰው በ12/03/2015 እንደገና ከፍተኛው ፍርድ ቤት በCommittal hearing ላይ ቀርበው እንደነበር ከአሁን በፊት መገለጹ ይታወሳል።

በ12/03/2015 የዋለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የCommittal hearing ችሎት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አለመፈጸም እስከ 2 ዓመት በሚያደርስ እሥራት እንደሚያስቀጣ ለተከሳሾቹ (አባ ግርማ ከበደና ተከታዮቻቸው) በማስረዳት ሆኖም ግን የፍርድ መተላለፉን ወንጀል በፈጸሙት ላይ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ሕግ በሚፈቅድላቸው መሠረት ሕጋዊ እውቅና ባለው ጠበቃ (Professional Lawyer) መወከል ስላለባቸው ከፍያው በመንግሥት ድጎማ (Legal aid) የሚሸፈን ጠበቃ እንዲይዙ የ15 ቀን ጊዜ በመስጠት ቀጣዩ የፍርድ ቤት Committal hearing ችሎት በ26/03/2013 እንዲሆን በመወሰን አሰናብቶአቸው ነበር።

በዚህም መሠረት ሐሙስ 26/03/2015 በእንግሊዝ ሃገር ታዋቂ በሆነው ፍርድ ቤት (The Royal Court of Justice) የቤተ ክርስቲያኑ አባላት የሆኑት አመልካቾችና ተከሳሾቹ አባ ግርማ ከበደና ሌሎች 8 ተከታዮቻቸው በሃገሩ አቆጣጠር ከጠዋቱ 10:30 ሰዓት ጀምሮ ፍርድ ቤቱ ችሎት ላይ በመቅረብ በጠበቆቻቸው አማካኝነት ጉዳያቸው ለዳኛው ሊቀርብ ችሏል።

The Royal Court of Justice



የተሰየሙት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛም በ12/03/2015 ጉዳዩን ያዩት ዳኛ ስለነበሩ ያለፈውን በማስታወስ በ13/02/2015 ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያወጣው ትዕዛዝ (Court order) አለመፈጸሙን ተከሳሾቹ ካቀረቡት የጽሑፍ እምነት ክህደት ቃል (Affidavit) ሊረዱ እንደቻሉ በመግለጽ በጉዳዩ ላይ ከሁለቱም ወገን ጠበቆች በየተራ የቀረበውን መከራከሪያ ነጥብ በጥሞና ካዳመጡ በኋላ የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ላለመፈጸም አባ ግርማና ተከታዮቻቸው ያቀረቡትን የተለመደውን ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ይጣሳል የሚለውን ማደናገሪያ የሃሰት ሰበብ ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ ጋር የሚያገናኘው ነገር እንደሌለ በማረጋገጥ ተከሳሾቹ የፍርድ ቤትን ትዕዛዝ መተላለፍ (Contempt of Court) ወንጀል በጋራና በተናጠል መፈጸማቸውን በማረጋገጥ የፍርድ ውሳኔ ወደ ማስተላለፍ ተሸጋገሩ።

የተከበሩት ዳኛም የፍርድ ቤት ውሳኔ በሌላ ከፍተኛ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ሆነ በSupreme court እስካልተሻረና ተፈጻሚ አይሁን (stay from execution) የሚል ብይን እስካልተላለፈበት ድረስ ያለምንም ምክንያትና ማወላወል መፈጸም ስላለበት የተሰየመው (Committal hearing) ችሎት የመጀመሪያ ሥራው ትዕዛዙን ማስፈጸምና ትዕዛዙን ባልፈጸሙት ላይ ቅጣት ማሳለፍ መሆኑን ከገለጹ በኋላ የሚከተለውን ጥያቄ ለአመልካቾች (የቤተ ክርስቲያኑ አባላት) ጠበቃ አቀረቡ። የዳኛውም ጥያቄ፡ የፍርድ አመልካቾቹ (የቤተ ክርስቲያኑ አባላት) የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ወደፊት ተፈጻሚ እንዲሆን በማድረግ መብታቸው ከመከበሩ በተጨማሪ ትዕዛዙን ባለማክበር ወንጀል በፈጸሙት አባ ግርማ ከበደና ተከታዮቻቸው (በድምሩ 9 ሰዎች) በእሥር (Custodian sentence) መቀጣታቸውን የሚፈልጉ ከሆነ እንዲገልጹ በማለት ጠየቁ።

በመቀጠልም የአመልካቾቹ ጠበቃ ይህንን መልስ ለመሥጠት ከደንበኞቹ (Clients) ጋር የመምከሪያ ጊዜ እንዲሰጠው በመጠየቃቸው ዳኛው ለተወሰነ ደቂቃ ችሎቱ ተቋርጦ እረፍት እንዲደረግ አዘዙ።

በዚህ ጊዜ እውነትን ይዘው ለሃይማኖታቸው፤ ለቤተ ክርስቲያናቸውና ለፍትሕ ጸንተው በመቆም ለሁለት ዓመት መከራና ችግር የተፈራረቀባቸው የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ይህንን ሁሉ ችግር ያደረሱባቸውን አባ ግርማ ከበደም ሆኑ ተከታዮቻቸው መራራውን የእሥር ቅጣት እንዲቀበሉ ይወስኑባቸዋል ተብሎ ሲጠበቅ እነሱ ግን የበቀልንና የክፋትን መንገድ በመናቅ የክርስቶስ ተግባር የሆነውን የክርስትናን መንገድ በመከተል ክፋትን በክፋት እና በደልን በበደል ላለመመለስ በፍርድ ቤት የተረጋገጠላቸው መብታቸው እስከተከበረላቸው ድረስ የተከሳሾቹን መታሠር አንፈልግም በማለት አስገራሚ ምላሽ በጠበቃቸው አማካኝነት ለዳኛው አቀረቡ።

ዳኛውም የቤተ ክርስቲያኑ አባላት የሰጡትን ስብዕናን የተላበሰ ቅን መልስ በአድናቆት በመቀበል በተከሳሾቹ ላይ ሊፈርድ የነበረውን የእሥር ቅጣት በመተው ቀጥሎ የተመለከተውን የፍርድ ውሳኔ ሊያስተላልፍ ችሏል።

1) የቤተ ክርስቲያኑ ህንጻ እና በግቢው ውስጥ ያለው የመኖሪያ ቤት (የቪካሬጅ ህንፃ) ቁልፎች ሁሉ Look Smith በተባለው ቁልፍ ለዋጭ ድርጅት አማካኝነት እንዲቀየር፤
    - የቁልፍ መለወጡ ተግባርም ፖሊስ እና የአመልካቾች ጠበቃ፤ እንዲሁም የአመልካቾች ሁለት ተወካዮች በተገኙበት እንዲፈጸም፤
    - የቁልፉ መለወጥም 24 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንዲከናወን፤
2) የቤተ ክርስቲያኑ አባላት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ተፈጻሚ አላደርግም ያሉትን እነ አባ ግርማን ለCommittal hearing ለማቅረብ ያወጡትን የሕግ ወጪ ሁሉ 9ኙ ተከሳሾች እንዲከፍሉ፤

ብሎ በመወሰን ከዚህ በተጨማሪ የወጣውን የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ላማደናቀፍና ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ለማድረግ በሚሞከሩ ላይ ጥብቅ እርምጃ እንደሚወሰድ በማሳሳሰብ ፍርዱን አጠናቀቀ።

ዳኛው ፍርዱን አስተላልፎ እንደጨረሰም መቸም ደንብ ነውና የተከሳሾች ጠበቃ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ እንዳለው አስታውቆ ዳኛው የይግባኙን መሠረት (Ground) እንዲገልጽ ጠይቀውት ካብራራ በኋላ ዳኛው በሁለት ደረጃ የቀረበውን የይግባኝ ጥያቄ ውድቅ አድርገውት የፍርዱ ውሳኔ እንዲጸና ተደርጎ የፍርድ ቤቱ ሂደት ተጠናቋል።

በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት በ27/03/2015 በዕለተ ዓርብ 1400 ሰዓት አካባቢ ፖሊስ፤ የአመልካቾች ጠበቃ ከአመልካቾች ተወካዮች ጋር የ Look Smith ሰራተኛውን በመያዝ ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ሲደርሱ አባ ግርማ ከበደን ከካሜራ ምድብተኞች ጋር አገኟቸው።



የፖሊስ ኢንስፐክተሩም በተሰጠው መመሪያ መሠረት አባ ግርማን ቀርቦ የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ደርሷቸው እንደሁ ሲጠይቃቸው ከአሁን በፊት መልዕክተኛው ፊትለፊት ቆመው የለሁም (I am not available) እንዳሉት ሁሉ አሁንም ማምለጫ መስሏቸው የደረሳቸውን የፍርድ ቤት ማዘዣ አልደረሰኝም በማለት ካዱ።

አባ ግርማ ከበደ ለፖሊሱ ኢንስፔክተር በመዋሸትና በመካድ ላይ እያሉ የተነሳ ምስላቸው።



የፖሊስ ኢንስፐክተሩ ግን የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ በእጁ ይዞ ስለነበር ወዲያውኑ በእጃቸው ሲሰጣቸው ተቀብለው እንደቆሙ በሩ ሳይከፈት ቁልፉ ለመቀየር ከመሞከር ቢከፈትና ቢቀየር ስለሚቀል በሩን ለመክፈት ፍቃደኛ ከሆኑ በማለት ሲጠይቃቸው አልከፍትም ብለው አሻፈረኝ ስላሉ ፖሊሱ ቁልፍ ቀያሪው የተዘጋውን በር ባለው ዘዴ ከፍቶ ቁልፉን እንዲቀይር መመሪያ ሰጠ።

ፖሊሶች የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ሲያስፈጽሙ።



በዚህ መሠረት ከ7 ያላነሰ የህንፃ ቤተ ክርስቲያኑና የቪከሬጅ ህንፃው በሮች ቁልፎች ሙሉ በሙሉ ተቀይረው ቤተ ክርስቲያኗ አዲስ መገልገያ ቁልፍ እንዲኖራት ከተደረገ በኋላ ለመብታቸውና ለፍትሕ ቆመው ለሚታገሉት የቤተ ክርስቲያኑ አባላት መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት ላለፉት 2 ዓማታት ሲደክሙና በሃሰተኞች መከራ ሲወርድባቸው የኖሩት መላዕከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት ከዲያቆን ደረጀ ሞገስ ጋር በመሆን የፖሊስ ኢንስፐክተሩንና የተወከለውን ጠበቃ በመያዝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተው እንዲያዩ የተደረገ ሲሆን ለካህናት ብቻ የተፈቀደውንም አካባቢ ካህናቱ ብቻ ገብተው በማየት በቀጣዩ ቀን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የቅዳሴ አገልግሎት ለመሥጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች መሟላታቸውን እንዲያረጋግጡ ተደርጓል።

ይህ ሁሉ ከተከናወነና የሁሉም በሮች ቁልፍ መለወጡ ከተረጋገጠ በኋላ አባ ግርማ ከበደና ቄስ ብርሃኑ አንዳንድ ኮፒ ቁልፎች በፓሊሱና በጠበቃው ፊት እንዲረከቡ ተደርጓል።

ቄስ ብርሃኑ ብሥራት የቤተ ክርስቲያኑን ቁልፎች ከተረከቡ በኋላ ሕዝቡን ሲባርኩና ሕዝቡም ደስታውን ሲገልጽ።



የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ፈጣሪ ለዋለላቸው ውለታ የምስጋና ጸሎት ሲያደርሱ።




ይህ በተከናወነ ማግሥት ማለትም በ28/03/2015 በዕለተ ቅዳሜ በፍርድ ቤቱ የቤተ ክርስቲያኗን አጠቃቀም ድልድል መሠረት የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ተራ ስለነበር ቤተ ክርስቲያኗ ከጠዋቱ 0700 ሰዓት ጀምሮ በቄስ ብርሃኑ ብሥራት አማካኝነት ተከፍታ ሥጋዊ ጥቅምን ሲሉ ክህደት በፈጸሙባቸው  ጥቂት እብሪተኛ ካህናት ምክንያት ለሁለት ዓመት

ከ17 ቀን ከቤተ ክርስቲያናቸው ወጥተው ከቅዱስ ታቦቱና ከቁርባን እርቀው ብርድ፤ ዝናብ፤ በረዶና ንፋስ እየተፈራረቀባቸው በውጪና በድንኳን ውስጥ ሲጸልዩ የኖሩት ካህናትና ምእመናን ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ በእንባ እየተራጩ ቤተ ክርቲያናቸው ውስጥ በመግባት ሙሉ የቅዳሴና የቁርባን ሥርዓት ለማካሄድ ችለዋል።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዕለቱ የቅዳሴ አገልግሎት ሲጀመር።



ካህናቱ በቅዳሴ መሃል



ካህናቱና ምእመናኑ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ የወንጌል ስብከትን ሲከታተሉ።





**ምንም የማይሳነው ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው!!**

**ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንን እናድን ማህበር።**

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!**